# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWENTY-TWO: « የወንዶችንግግር»

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: አቶ ጃለታ HAS A WORD WITH ንጉሴ AT HOME**

- ንጉሴ ንጉሴ **(M, 15)**
- አቶ ጃለታ **(M, 45)**

**SCENE 2: አቶ ካሳሁን AND ዳንኤል HAVE DINNER**

- አቶ ካሳሁን **(M, 55)**
- ዳንኤል **(M, 16)**

**SCENE 3: አቶ ሙላቱ ARRIVES IN THE VILLAGE LATE IN THE EVENING**

- አቶ ሙላቱ **(M, 45)**
- አቶ ገረመው **(M, 75)**
- ወ/ሮ ፀሀይ **(F, 65)**
- ወ/ሮ ሉሊት **(F, 40)**

## SCENE 4: POLICE LOOK FOR አቶ ሙላቱ AT NIGHT

- ምህረት (F, 15)
- OFFICER 1 (M/F, ?)
- OFFICER 2 (M/F, ?)

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ የሚቀርብላችሁ ድራማ ነዉ። ለማስታወስ ያህል፦ምህረት ከክፍል ጓደኛዋ ንጉሴ ደብዳቤ ደርሷታል። በደብዳቤውም አባቷ አቶ ሙላቱ እንዲጠነቀቁ ነግሯታል። ወላጆቹ ቀደም ሲል ቤታቸውን ይጠብቁላቸው የነበሩትን አቶ ሙላቱ ማለትም የምህረት አባትን በዘረፋው እጃቸው አለበት ብለው ይጠረጥሩዋቸዋል።

2. **ምህረት (EP 21, 44):** “አባዬ. (...)አንድ ሰው ይህንን ማስታወሻ ሰጠኝ። የሚለውም አንተ በዘረፋ ወንጀል ውስጥ እንዳለህበት ነው።...?”

3. **አቶ ሙላቱ (47):** “ማን አባቱ ነው ደግሞ እንዲህ የሚለው...?!”

4. **ምህረት (50):** “ፖሊሶች በቅርቡ ሊመጡ ስለሚችሉ ምናልባት ... (...)ወደ እማዬ ወላጆች ጋ መሄድ ትችላለህ። ገጠር ትሄዳለህ ብሎ ማንም ሰው አያስብም።”

የዚያኑ ምሽት አቶ ሙላቱ ቤቱን ለቀው ወደ ባለቤታቸው ወ/ሮ ሉሊት ቤተሰቦች አምርተዋል። ግን ወ/ሮ ሉሊት ከሳቸው ተጣልተው ነው የሄዱት ታድያ ባለቤታቸው ሊቀበሏቸው ፍቃደኛ ይሆኑ ይሆን?

በሌላ በኩል የምህረት ፍቅረኛ ዳንኤል ሳያስበው እንግዳ መጥቶበታል።:

5. **SFX: ዳንኤል SCORES (EP 21, 104)**

6. **SFX (108): CLAPPING OF HANDS**

7. አቶ ካሳሁን: “ይሄ ነው የኔ ልጅ። ምን ያህል ጠንካራ እንደሆንክ አሳያቸው”

8. ዳንኤል : “አባዬ እዚህ ምን ታደርጋለህ?”

የዳንኤል አባት ረዥም ጉዞ አድርገው ከላቦሪያ ያለበት ድረስ መጥተዋል። እዛ ድረስ መሄድ ያስፈለጋቸው ለምን ይሆን? ንጉሴም ከአባቱ አቶ ጃለታ ጋ መነጋገር ግድ ይለዋል። ወላጆቹ እክፍሉ ሆኖ ሲጋራ ሲያጨስ ደርሰውበታል። ከትምህርት ቤት ሲመለስ አባቱ ስለዚህ ጉዳይ ከንጉሴ ጋ ሊወያዩ ይፈልጋሉ። እንግዲህ በዚህ ነው የዛሬውን 22ኛ ክፍል ጭውውት የምንጀምረው። ርዕሱ« የወንዶችንግግር» ይሰኛል።

## SCENE 1: አቶ ጃለታ HAS A WORD WITH ንጉሴ AT HOME

7. **SFX: አቶ ጃለታ SWITCHING TV CHANNELS**

8. **SFX: FRONT DOOR BEING UNLOCKED, OPENED AND CLOSED**

9. አቶ ጃለታ: **(firmly)** ሰላም ንጉሴ። በል ቦርሳህን አስቀምጥና እዚህ ጋ መጥተህ ተቀመጥ። ላነጋግርህ እፈልጋለሁ።

10. **SFX: TV TURNED OFF**

11. ንጉሴ: **(not amused)** ጉዳዩ ምንድን ነው?

12. አቶ ጃለታ: ካንተ ጋ መጨቃጨቅ አልሻም ንጉሴ። መነጋገር አለብን። ችግር አትፍጠር።

13. **SFX: SCHOOL BAG THROWN DOWN**

14. አቶ ጃለታ: **(trying to control temper)** ቦርሳህን አስቀምጥ እንጂ ወርውር አላልኩህም። ተቀመጥ አሁን።

15. **SFX: ንጉሴ SITS DOWN HEAVILY ON THE SOFA**

16. ንጉሴ : እሺ እየተቀመጥኩ አይደል እንዴ። እ ምንድን ነው?

**17.** አቶ ጃለታ: **(politely)** ንጉሴ , መቼ ነው ሲጋራ ማጨስ የጀመርከው?

**18.** ንጉሴ : ዛሬ ጠዋት።

**19.** አቶ ጃለታ: **(doubting)** የምሬን ነው ንጉሴ! ንገረኝ። ስንት ጊዜ ሆነህ?

**(short pause )**

**20.** ንጉሴ : **(very casual)** ያን ያህል ረዥም ጊዜ አይደለም። ምንአልባት ጥቂት ሳምንታት።

**21.** አቶ ጃለታ: ጥቂት ሳምንታት? ምን ማለት ነው? ሶስት? አስር ወይንስ ሀምሳ ሳምንታት?

**22.** ንጉሴ : ሶስት ሳምንት

**23.** አቶ ጃለታ: **(swallows hard)** እሺሺሺ … ምን ነበር ስታጨስ የነበረው?

**24.** ንጉሴ : አባዬ። ሲደብረኝ ብቻ ነው የማጨሰው።

**25.** አቶ ጃለታ: የጠየኩህን መልስ ንጉሴ። ከሲጋራ ሌላ ፤ ሌላ ሱስ አስያዥ ነገር ታጨሳለህ?

**26.** ንጉሴ : እንደዛ እንኳን አይባልም።

**27.** አቶ ጃለታ: **(getting angry)** ግማሽ መልስ መመለስህን አቁም ንጉሴ ! ትዕግስቴን እያስጨረስከኝ ነው። እውነቱን ንገረኝ።

**28.** ንጉሴ : **(bitterly)** እውነቱማ አባዬ፣ ለእኔ ምንም ደንታ የለህም። አንተን የሚያስጨንቅህ ነገር ቢኖር ገንዘብ ነው። በየጊዜው ትርፍ፣ ማግኘት።

**29.** አቶ ጃለታ: **(surprised)** ልክ አይደለም እያልክ ያለኸው። ስላንተ እጨነቃለሁ።አሁን ከአንተ ጋ ቁጭ ብዬ የምወያየው ለምን ይመስልሀል?

**30.** ንጉሴ : እማ ስለጠየቀችህ ብቻ ነው።

**31.** አቶ ጃለታ: ዋናው ነገር እሱ አይደለም። እኛ ወላጆችህ ነን። ለአንተ በጎውን ነው የምንመኝው። አሁን እውነቱን ንገረኝ። ለምንድን ነው ማጨስ የጀመርከው? አሁን እናትህም ሆነች እኔ እንደው አናጨስ።

**32.** ንጉሴ : ምክንያቱ ምን ያደርግልሀል። ማወቅ የነበረብህን ነግሬሀለሁ። አሁን ወደ ክፍሌ መሄድ እችላለሁ? ማጥናት አለብኝ።

**33.** አቶ ጃለታ: **(sarcastic)** ማጨስ አለብኝ እያልክ ነው?

**34.** ንጉሴ : አየህ ለዚህ ነው ምንም ነገር የማልነግርህ። በፍፁም አትረዳኝም።

**35.** አቶ ጃለታ: ስማኝ ንጉሴ። ይህንን መጥፎ ልማድ አሁኑኑ እንድታቆም እፈልጋለሁ። ሰማኸኝ አሁኑኑ! ለጤንነትህ ጥሩ አይደለም። ሱሰኛ ነው የምትሆነው በዛ ላይ ጎጂ ነው። ስለዚህ አሁኑኑ ማጨስ ብታቆም ይሻልሀል ፤ በኋላ ሰዉ ልጃችሁ እንደ ወንጀለኛ ጭሱን ቡልቅ እያደረገ በየመንገዱ ይሄዳል ሳይል።

**36.** ንጉሴ : አሁን መሄዴ ነው።

**37.** አቶ ጃለታ: **(puzzled)** ንጉሴ ቁም ብያለሁ። ምንድን ነው የሆንከው። ጥሩ ልጅ አልነበርክም እንዴ? እዚህ ቦንጎ አካዳሚ ከገባህ ወዲህ ተለውጠሀል። ቢነግሩት የማይሰማ፣ የማይታዘዝ እና ኋላፊነት የጎደለው ሆነሀል!

**38.** ንጉሴ : በእውነት? ታድያ አንተ እንደምትለኝ ከሆንኩማ፤ ለምን የክፍል አለቃ ሆኜ ተመረጥኩ?

**39.** አቶ ጃለታ: **(takes deep breath)**

**40.** ንጉሴ: **(sarcastic)** አየህ? አመሰግናለሁ አሁን ወደክፍሌ መሄድ እችላለሁ?

**41. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 2: አቶ ካሳሁን AND ዳንኤል HAVE DINNER

**42. SFX: RESTAURANT ATMO**

**43.** አቶ ካሳሁን: ፀጥተኛ ሆንክ እሳ ዳንኤል። እስቲ ንገረኝ ትምህርት እንዴት ነው?

**44.** ዳንኤል: **(with a mouthful)** እእእ ብዙም አዲስ ነገር የለም። የት እንደምተኛ አየህ አይደል።...

**45.** አቶ ካሳሁን: አዎ አየሁት። በእውነቱ መጠን ያለ ኑሮ እንድትኖር እያስተማሩህ ነው። **(laughs)** እስር ቤት በመሰለች ጠባብ ክፍል እያኖሩህ እኔን ለምን ያን ያህል ገንዘብ ለት/ቤት እንደሚያስከፍሉኝ አይገባኝም።

**46.** ዳንኤል : **(meekly)** ተመችቶኛል።

**47.** አቶ ካሳሁን: ጥሩ። ዋናው ነገር ይሄው ነው። እስቲ ደግሞ ትንሽ አጫውተኝ። የዚህች ልጅ ነገርስ ልታስተዋውቀኝ አትፈልግም?

**48.** ዳንኤል : የትኛዋን ልጅ ነው የምትለው አባዬ? ምንም አይነት ልጅ የለችም። ከቤት ወደ ሌላ ሀገር የላከኝ ከጓደኞቼ እንድርቅ ፣ እዚህ ለእኔ ይሻላል ብለህ አይደል? ... ልክ ነበርክ።

**49.** አቶ ካሳሁን: **(curious)** ጓደኞችህ ጥሩ ልጆች አልነበሩም ዳንኤል ! ወዳልሆነ አቅጣጫ እየመሩህ ነበር። ለዚህ ነው ወደዚህ የላክንህ። የቤተሰቡን ድርጅት ለመረከብ የሚያስችል ስልጠናም ታገኝበታለህ።

**50. SFX: CUTLERY BEING PUT DOWN**

**51.** ዳንኤል: **(deep breath)** ጀመረህ እንግዲህ ... ለዚህ ጉዳይ ነው እዚህ ድረስ የመጣኸው አባዬ። የማዕድኑን ድርጅት እንድረከብህ ለአንድ ሚሊዮንኛ ጊዜ ልታሳምነኝ?

**52.** አቶ ካሳሁን: አይደለም ነግሬሀለሁ።ያለህበትን ሁኔታ ለማየት ስል ነው የመጣሁት ዳንኤል … የአንተ ደህንነት ያሳስበኛል። በዛ ላይ … አልማዝ ልትጠይቀኝ መጥታ ነበር። ስለአንተም ሀሳብ ገብቷት ነበር። እንደዛ ስታዝን ደግሞ ማየት አልፈልግም። በዛ ላይ እሷ የቅርብ የሆነ የንግድ ባልደረባችን ልጅ ነች። ሁለታችሁ ደግሞ ድስት እና ክዳን ናችሁ።

**53.** ዳንኤል : ታውቃለህ አባዬ? የአልማዝ ጉዳይ አያስጨንቀኝም። ከአለም ውብ የሆነች ልጅ ተዋውቄያለሁ። እና አባዬ ተገቢውን ክብር እየሰጠሁህ፤ በእውነት በሕይወቴ ውስጥ ጣልቃ ባትገባ ደስ ይለኛል።

**KW BEGIN**

**54. SFX: DRINK POURED INTO A GLASS**

**55.** አቶ ካሳሁን: **(after sipping drink)** ጣልቃ እየገባሁ አይደለም። የአቋቋምኩትን ለመጠበቅ እና ለማቆየት ነው። ኪሲንባ ያሉ ልጆችን እየተመለከትክ እንደሆነ ይገባኛል። ግን ይህቺ ልጅ ለአንተ አትሆንህም። ከቤተሰቦችህ እና ከሀገርህ ታርቅሀለች።

**56.** ዳንኤል: **(hits back)** አታርቀኝም። እሷን አልተዋወካት። እንዴት አስቀድመህ ፍርድ ትሰጣለህ?

**57.** አቶ ካሳሁን: **(with resignation)** ወይ! ዳኒ ዳኒ ልጄ ለምንድን ነው እንደዚህ አስቸጋሪ የምትሆነው? ነገሮች ቀላል ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ግን አንተ ሊገባህ አልቻለም። እኔም በአንድ ወቅት በአንተ እድሜ እንደነበርኩ ትረሳዋለህ። ምን እንደሚመስል አሳምሬ አውቀዋለሁ። ነገር ግን ድርጅቱ ይፈልገሃል። አንተም ትፈልገዋለህ።

**58.** ዳንኤል : **(firmly)** አባዬ አታዳምጠኝም ልበል። ምንም ይሁን ምን ያንተ ድርጅት ጨርሶ አያሳስበኝም።

**KW END**

**59.** አቶ ካሳሁን: **(also firmly)** ዳንኤል፤ ወደ ቤተሰቡ ድርጅት አልቀላቀልም አሻፈረኝ ልትል ትችላለህ። ነገር ግን እኔም የውጭ ሀገር ሰው ቤተሰቤን እንዲቀላቀል እንደማልፈልግ ትረዳኛለህ ብዬ አገምታለሁ። እዚህ ካለቺው ልጅ ጋ የጀመርከውን አሸሼ ገዳሜ አርግፍ አድርገህአብረኸኝ ወደቤታችን እንድትመጣ ነው የምመክርህ።ከዛም ከአልማዝ ጋ አብራቹህ ትሆናላችሁ። አሁን ወደ ሆቴል ሄጄ አረፍ ልበል። ማሰብ ስትችል ነገ እንነጋገራለን።

**60. SFX: CHAIR PUSHED BACK**

**61. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 3: አቶ ሙላቱ ARRIVES IN THE VILLAGE LATE IN THE EVENING

**62. SFX: EVENING ATMO IN THE VILLAGE**

**63. SFX: FOOTSTEPS WALKING**

**64.** አቶ ሙላቱ : **(exhausted, to himself)** ሙላቱ ይሀ ጥሩ ሀሳብ አልነበረም። እሺ አሁን ይኸው እመንደሩ ደረስኩ እሺ ታዲያ አሁን ባለቤቴን ምን ልላት ነው? **(acts out)** " ሉሊት , ውዷ ባለቤቴ መጣሁልሽ። …" **(back to thoughts)** የለም ይሀ የማይረባ አባባል ነው።! **(another act)** "ሉሊትዬ በጣም ስትናፍቂኝ ጊዜ አንቺ ዘንድ ለመምጣት ወሰንኩ።" **(back to thoughts)** ወይ ዕዳ… ይሻላል። ግን አሁንም በቂ አይደለም። ምናልባት እውነቱን ብነግራት ይሻላል። **(acts again)** " ሉሊት ፖሊሶች እየፈለጉኝ ነው። እና ሌላ የምሄድበት ቦታ ስለሌለኝ ወደአንቺ መጥቻለሁ።" **(back to thoughts)** ትረዳኛለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።…

**65. SFX: LAUGHTER FROM INSIDE THE HUT/ ወ/ሮ ሉሊት VOICE HEARD TOO**

**66.** አቶ ገረመው : **(from inside the hut, coughing slightly)** በርግጥ የሆነ ታሪክ እኮ ነው የምነግርሽ። እመኚኝ ልጅ ፀሀይ። ንገሪያት ያኔ ገና ልጅ ነበረች። **(continues to cough)**

**67.** ወ/ሮ ፀሀይ : **(from inside hut)** ሉሊት ፤ እስቲ እባክሽ ለአባትሽ የሚጠጣ ውሃ አምጪለት። ሳሉ አልተሻለውም።

**68.** ወ/ሮ ሉሊት : **(from inside hut)** እሺ እማዬ

**69. SFX: WOODEN DOOR BEING OPENED AND CLOSED**

**70.** አቶ ሙላቱ : **(gently)** ሉሊት …

**71.** ወ/ሮ ሉሊት: **(screams in fear)** ውይ!

**72.** አቶ ሙላቱ : ሉሊት እኔ ነኝ ሙላቱ። ባለቤትሽ። ይቅርታ ላስደነግጥሽስ ብዬ አልነበረም።

**73.** አቶ ገረመው: **(from inside)** ሉሊት ፤ ምንድን ነው? ምን ሆነሻል? የሉሊት እናት እረ እስቲ ሂጂና ልጃችን ምን እንደሆነች ተመልከቺ።

**74. SFX: DOOR BEING OPENED AGAIN**

**75.** ወ/ሮ ሉሊት : **(still shocked)** ሙላቱ ? ከየት ነው የምትመጣው። ምህረት የታለች? ለምንድን ነው ብቻህን የመጣኸው?

**76.** ወ/ሮ ፀሀይ: **(unfriendly tone)** ሙላቱ፤ እዚህ ምንታደርጋለህ? አንተ ሰካራም።

**77.** ወ/ሮ ሉሊት : ቆይ እማ ! እኔ አነጋግረዋለሁ።

**78.** አቶ ሙላቱ : የ ሉሊት እናት እንደምን አሉ። እንዴት ሰንብተዋል?

**KW BEGIN**

**79.** ወ/ሮ ፀሀይ: **(furious)** ከዚህ ቤት ውጣ። እርጉም! ልጃችንን ለአንተ የሰጠን ቀን ነው የተረገምነው። ውጣ እዚህ ልናይህ አንፈልግም።

**80.** ወ/ሮ ሉሊት **:** እማማ ይበቃል። ሙላቱ አሁንም ባለቤቴ እና የልጆቼ አባት ነው።

**81. SFX: WATER BEING FETCHED WITH A JERRY CAN**

**82.** ወ/ሮ ሉሊት : ለአባዬ የሚጠጣው ውሃ ይሄውልሽ። ከሙላቱ ጋ ለመነጋገር ጥቂት ጊዜ እፈልጋለሁ።

**KW END**

**83.** ወ/ሮ ፀሀይ **:** እሺ… ተመልሼ ወደ ውስጥ እገባለሁ። ግን ልጄ ሲያስፈራራሽ ዝም አልለውም።

**84. SFX: STEPS BACK TO THE HUT, WOODEN DOOR CLOSED**

**85.** ወ/ሮ ሉሊት **:** እሺ ሙላቱ። ምንድን ነው ልትነግረኝ የፈለከው?

**86. MUSIC TRANSITION**

**<u>SCENE 4: POLICE LOOK FOR</u>** <u>አቶ ሙላቱ</u> **<u>AT NIGHT</u>**

**87. SFX: NIGHT ATMO, LOUD KNOCK ON DOOR**

**88. OFFICER 1: (from outside, ordering)** ፖሊሶች ነን። በሩን ክፈቱ። እደግመዋለሁ። በሩን ክፈቱ።

**89. SFX: LOUD KNOCKING CONTINUES…**

**90.** ምህረት **: (scared voice from inside)**

**91. SFX: DOOR BEING UNLOCKED**

**92. OFFICER1: (shouts)** የት ነው ያለው? አባትሽ የት ነው ያለው? በወንጀል ስለተጠረጠረ በቁጥጥር ስር ልናውለው ነው።

93. ምህረት : አባዬ እዚህ የለም እርሱ --

94. OFFICER1: (shocked) ምን? ከበሩ ላይ ዞር በይ።

95. SFX: ምህረት PUSHED ASIDE AND FALLING DOWN

96. ምህረት : (cries in pain) አአአአ በእውነት ነው የምላችሁ እዚህ የለም።

97. OFFICER 1: አንድ ቦታ ተደብቆ ይሆናል (orders colleague) መርማሪ!

98. OFFICER 2: አቤት ጌታዬ!

99. OFFICER 1: ቤቱን በደንብ አድርገህ ፈትሽ። በደንብ ስል በደንብ ነው።

100. OFFICER 2: አሁኑኑ ጌታዬ!

101. SFX: THINGS BEING THROWN AROUND, BOOKS FALLING, GLASSES BREAKING ETC

102. ምህረት: (pleading) አባክዎ ይተዉ! በእውነት ነው የምላችሁ እዚህ የለም። እነሱ የትምህርት ቤት መፅሀቴ ናቸው ይተው።

103. OFFICER: እና የት ነው ያለው?

104. ምህረት : (crying) አኔንጃ።

105. MUSIC INTERLUDE

## 106. OUTRO - NARRATOR:

ምህረት  የምታደርገው ጠፍቷት ፖሊሶች የቤተሰቧን ዕቃ ሲያመሰቃቅሉ ቆማ ትመለከታለች። አባቷ ብቻ በጊዜ ገጠር ገብተዋል ብላ ብቻ ነው ተስፋ ማድረግ የምትችለው። ግን ወ/ሮ ሉሊት ይረዷቸው ይሆን ወይንስ ሂድልኝ ይሏቸዋል? በሚቀጥለው ክፍል እንደርስበታለን።   ከዚህ በፊት የነበሩ ክፍሎች አምልጧችሁ ከነበረ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን በመጎብኘት ደግመው ሊሰሙ ወይንም ያለክፍያ ኮምፒተርዎ ላይ ሊፅኑ ይችላሉ። እዚያን ላይ የዳንኤልን የቪዲዮ የቀን ዘገባ ያገኛሉ። በሚቀጥለው ጊዜ እንደምንገናኝ ተስፋ እያደረግን እስከዚያው ጤና ይስጥልን።